
# The CAMBRIDGE LIFE

CAMBRIDGEMA.GOV/DIGITAL

በልግ 2022 A PUBLICATION OF THE CITY OF CAMBRIDGE, MASSACHUSETTS



## በካምብሪጅ ውስጥ የሚገኙ ተጋላጭ ማህበረሰቦችን መደገፍ

A
ድሆችን በመደገፍ ላይ ታሪካዊ እይታ
ገጽ 8


ከአዲሱ የከተማ አስተ ዳዳሪ Yi-An Huang ጋር የተካሄደ የጥያቄ እና መልስ ቆይታ

የከተማዋ ሰራተኞች ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ወሳኝ ድጋፎችን በመስጠት ላይ

ነዋሪዎች ያሉባቸውን ተግዳሮቶች ይፈቱ ዘንድ ከMulti-Service Center (የብዙ አገልግሎ ቶች ማዕከል) ሰራተኛ የሚቀርብ ድጋፍ።

ወረርሽኙ የምግብ ድህ ንነትን የሚያረጋግጡ አዳዲስ አቀራረቦች እን ዲኖሩ አነሳስቷል

የብዙ ቋንቋዎች ዳሰሳ ገጽ 14-20

# በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርብ የመኖሪያ ቤት ወፍ በርር እይታ

**The U.S. Department of Housing and Urban Development (HUD) ( (የተባበሩት የአሜሪካ መንግስታት የቤቶች እና የከተማ ልማት) በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርብ ቤትን አንድ ቤተሰብ ከቤት ጋር ተያይዘው ለሚመጡ ወጪዎች፣ ይህም የቤት ኪራይን ወይም ብድር እና የአገልግሎት ክፍያዎችን ጨምሮ የሚከፍልተት ክፍያ ከአጠቃላይ ወርሃዊ ገቢያቸው ከ 30% ያልበለጠ ሲሆን ነው ብሎ ጠቅለል አድርጎ ይገልጸዋል። አንዳንድ መርሃ-ግብሮች ተከራዮች ከአጠቃላይ ወርሃዊ ገቢያቸው ውስጥ ለቤት ጉዳይ ለሚወጡ ወጪዎች የሚውል 40% ክፍያ እንዲከፍሉ ሊጠይቁ ይችላሉ።**





*የ Frost Terrace እና Inman Crossing በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርበ የመኖሪያ ቤት ፎቶዎች* በRobert Benson Photography.

## ዘርፎች

**በፌደራል እና በግዛቶች ድጎማ የሚደርግላቸው የመኖሪያ ቤቶች** አንድ አመልካች የ Area Median Income (AMI) (የአካባቢ አማካይ ገቢ) እንዲኖረው ወይም ከአካባቢ አማካይ ገቢ 50% በታች የሆነ ገቢ እንዲኖረው ይጠይቃሉ። አንዳንድ መርሃ-ግብሮች የአንድ አመላካች ገቢ የ AMI 80% እንዲሆን ይፈቅዳሉ። አመልካቾች ምንም ገቢ የሌላቸው ሊሆኑም ይችላሉ።

**በገቢ ላይ የተመሰረተ የመኖሪያ ቤት።** ይህ ደግሞ አንድ አመልካች ዝቅተኛ እና ከፍተኛ የገቢ መጠን መመሪያዎችን እንዲያሟላ ይጠይቃሉ።

## ዓይነቶች

**ተንቀሳቃሽ ክፍል 8/ተከራይ ላይ የሚመሰረት ቫውቸር።** ይህ ድጎማ ተከራዩን የሚከተል ሆኖ በተባበሩት የአሜሪካ መንግስታት ውስጥ በየትኛውም ቦታልያ ጥቅም ላይ መዋል የሚችል ነው። አንድ ቫውቸሩን የያዘ ሰው በቤቶች ባለስልጣን/ኤጀንሲ ፈቃድ ወይም ማረጋገጫ የሚሰጠው ቤት ራሱ ፈልጎ ያገኛል።
**በመኖሪያ አከባቢ ላይ መሰረት ያደረገ የመኖሪያ ቤት/ህዝባዊ መኖሪያ ቤቶች** ሁሉም በህንጻው ወይም የልማት ቦታው ውስጥ የሚገኙ ክፍሎች ድጎማ የተደረገላቸው ናቸው። አንድ ተከራዮች የሚኖሩበትን ቤት ለቀው ከወጡ ድጎማው እነሱን አይከተልም።
**ፕሮጀክት ላይ መሰረት ያደረገ የመኖሪያ ቤት።** አንዳንድ በህንጻው ውስጥ የሚገኙ ክፍሎች ድጎማ የሚደረግላቸው ናቸው፣ መላው ህንጻ ግን ድጎማ የሚደረግለት አይደለም። ከመኖሪያ አከባቢ መሰረት የሚያደርግ ወይም ህዝባዊ የመኖሪያ ቤት ጋር ተመሳሳይ በሆነ መልኩ፣ ተከራዮቹ ቤቱን ለቀው ከሄዱ፣ ምንም ዓይነት ድጎማ አይደረግላቸውም።
**Mass Rental Voucher Program (MRVP) (የማሳቹሴትስ የኪራይ ቫውቸር መርሃ-ግብር): ይህ ተንቀሳቃሽ/በተከራይ ላይ ወይም በፕሮጀክት ላይ መሰረት ያደረገ ሊሆን ይችላል።** ተንቀሳቃሽ የ MRVP ቫውቸር በMA ብቻ ላይ ነው ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው።

## ማነው

**የቤቶች ባለስልጣናት።** አብዛኛዎቹ በMA የሚገኙ ከተሞች የቤቶች ባለስልጣናት አላቸው። የቤቶች ባለስልጣናት ከHUD እና/ወይም ከMA Department of Housing and Community Development (DHCD) (የቤቶች እና የማሕበረሰብ ልማት ክፍል) ለቫውቸሮች እና የህዝባዊ መኖሪያ ቤቶች የሚሆን የገንዘብ ድጋፍ ያገኛሉ። የቤቶች ባለስልጣናት ቫውቸሮችን፣ በፕሮጀክት የገንዘብ ድጋፍ ላይ የተመረኮዘ መኖሪያ ቤቶችን የሚያስተዳድሩ ሲሆን የህዝብ ወይም በመኖሪያ አከባቢ ላይ መሰረት ያደረጉ የመኖሪያ ቤቶችንም ያለማሉ እንደዚሁም ይጠግናሉ።

**የቤቸች ኤጀንሲዎች።** በማሳቹሴትስ ውስጥ 9 Regional Administering Agencies (RAAs) (ክልላዊ አስተዳደር ኤጀንሲዎች) ይገኛሉ። እነዚህ ለትርፍ ያልተቋቋሙ ኤጀንሲዎች የተለያዩ የቤቶች ድጎማ መርሃ-ግብሮችን ያስተዳድራሉ። ከዚህም በተጨማሪ፣ የግዛቲቱን ገንዘባዊ ድጋፍ መርሃ-ግብር (Residential Assistance for Families in Transition; RAFT (በሽግግር ውስጥ ለሚገኙ ቤተሰቦች የሚሰጥ የመኖሪያ ድጋፍ)) ያስተዳድራሉ። Metro Housing|Boston ለካምብሪጅ ነዋሪዎች አገልግሎት የሚሰጥ ክልላዊ ኤጀንሲ ነው።

## በካምብሪጅ ውስጥ በተመጣጣኝ ዋጋ ቤት ለማግኘት የት እና እንዴት ማመልከት እንደሚቻል

ነዋሪዎች በካምብሪጅ ውስጥ እና በዙሪያዋ በተመጣጣኝ ዋጋ የመኖሪያ ቤት ለማግኘት ለምልቻው የሚገባቸው 5 ዋና ማመልከቻዎች አሉ።

- **Cambridge Housing Authority (CHA) (ካምብሪጅ የቤቶች ባለስልጣን)** ልተንቀሳቃሽ ክፍል 8 ቫውቸር እንደዚሁም ለካምብሪጅ በመኖሪያ ቦታ ላይ መሰረት ያደረገ እና ለካምብሪጅ ፕሮጀክት ላይ መሰረት ያደረጉ ክፍሎችን ለማግኘት በቀጠታ ወደ CHA ማመልከቻ ያስገቡ።**cambridge-housing.org/applicants**
- **CHAMP (Common Housing Application for Massachusetts Programs) (የጋራ መኖሪያ ቤቶች ማመልከቻ ለማሳቹሴትስ መርሃ-ግብሮች)** ለሁሉም በMA ውስጥ የሚገኙ በስቴቱ የገንዘብ ድጋፍ የሚደርግላቸው የህዝብ መኖሪያ ቤቶች የሚሆን በማዕከላዊነት የሚተዳደር ማመልከቻ። **camb.ma/CHAMP**

ቀጥሎ ያሉት 3 ማመልከቻዎች በMetro Housing|Boston ድረገጽ **metrohousingboston.org/apply-for-section.8** ላይ ሊገኙ የሚችሉ ናቸው።


- **ክልላዊ የመኖሪያ ቤት ማምልከቻ።** ለክፍል 8 ተንቀሳቃሽ ቫውቸሮች ወደ ሁሉም ክልላዊ የመኖሪያ ቤቶች ኤጀንሲዎች የሚሄድ አንድ ማመልከቻ።
- **በክልላዊ የመኖሪያ ቤት ፕሮጀክት ላይ መሰረት ያሚያደርግ ማመልከቻ።** በሜትሮ የመኖሪያ ቤቶች ክልል ውስጥ ለሚገኙ በፕሮጀክት ላይ መሰረት የሚያደርጉ የመኖሪያ ቤቶች ማመልከቻ ያስገቡ።
- **ማዕከላዊ የሆነ የክፍል 8 ማመልከቻ።** ወደ አብዛኛዎቹ በመላው ግዛቲቱ ውስጥ የሚገኙ የቤቶች ባለስልጣናት የሚሄድ አንድ ማመልከቻ። ወደ ካምብሪጅ አይሄድም- በቀጠተ ወደ CHA ማመልከቻዎን ያስገቡ።

ከዚህም በተጨማሪ፣ ገቢያቸው የ AMI 50% እና 120% የሆነ ነዋሪዎች፣ የ Cambridge Community Development Department (የካምብሪጅ የማሕበረሰብ ልማት መምሪያ) ሁለት በገቢ መሰረት የሚያደርጉ የኪራይ መርሃ-ግብሮች እና የቤት ባለቤትነት መርሃ-ግብሮችን ያቀርብላቸዋል። የበለጠ መረጃ ለማግኘት **cambridgema.gov/applyforaffordablehousing** ን ይጎብኙ።

## ማጠቃለያ

የመኖሪያ ቤት ለማግኘት ማመልከቻ ማስገባት ግራ የሚያጋባ እና የሚያስጭንቅ ሊሆን ይችላል። ከላይ ከተጠቀሰው መረጃ በተጨማሪ፣ ሌሎች መርሃ-ግብሮች እና የመኖሪያ ቤት ዕድሎች ሊኖሩ ይችላሉ። ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎን Office of the Housing Liaison (የቤቶች ግንኙነት ቢሮ) ን ፦ **Mpensak@cambridgema.gov** ላይ ኢሜይል በመላክ ያነጋግሩ።

# ማውጫ


ይህ አዲስ የፌደራል መርሃ-ግብር ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ቤተሰቦች ለአዲስ ወይም ለነባር የኢንተርኔት አገልግሎት የሚከፍሉት ክፍያ እንዲቀንሱ የሚያግዝ ነው።

## የ $30/ወር የኢንተርኔት ቅናሽ ዎን እያገኙ ነው?

ይህ አዲስ የፌደራል መርሃ-ግብር ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ቤተሰቦች ለአዲስ ወይም ለነባር የኢንተርኔት አገልግሎት የሚከፍሉት ክፍያ እንዲቀንሱ የሚያግዝ ነው። መስፈርቱን የሚያሟሉ ቤተሰቦች የመርሃ-ግብሩ ተሳታፊ ከሆነ አቅራቢ ላፕቶፕ ወይም ታብሌት በሚገዙበት ጊዜ አንድ ጊዜ ብቻ የ$100 ቅናሽ ያገኛሉ። ከነዚህ መርሃ-ግብሮች ውስጥ በአንዳቸው ላይ ተሳታፊ ከሆኑ፣ ወዲያው መስፈርቱን የሚያሟሉ ይሆናል፦

• SNAP • Medicaid • Federal Public Housing Assistance (የፌደራል ህዝባዊ የቤቶች ድጋፍ) • Lifeline • WIC • Supplemental Security Income • Veterans Pension/Survivor Benefits (የአርበኞች ጡረታ/ለተመላሾች የሚሰጡ ጥቅማ ጥቅሞች)

ለማመልከት፣ **AffordableConnectivity.gov** ይጎብኙ ወይም ወደ 1-877-384-2575 ይደውሉ።

Federal Communications Commission



2 ከአዲሱ የከተማ አስተዳዳሪ Yi-An Huang ጋር የተካሄደ የጥያቄ እና መልስ ቆይታ


6 የከተማ ማሕበራዊ ሰራተኞች



የምግብ ዋስትና አለመኖር 11


ነዋሪዎች ተግዳሮቶችን ይፈቱ ዘንድ መርዳት 10


የካምብሪጅ ፖሊስ በችግር ጊዜ ጣልቃ የመግባት ስልጠና 12


**2-3** ከአዲሱ የከተማ አስተዳዳሪ Yi-An Huang ጋር የተካሄደ ጥያቄ እና መልስ

**4-5** ከChristina Giacobbe በአዲሱ የከተማዋ Community Safety Department (የማህበረሰብ ደህንነት ክፍል) ጋር በተያያዘ የተደረገ የጥያቄና እና መልስ ቆይታ

**6-7** እጅጉን ተጋላጭ ለሆኑ የማህበረሰባችን አባላት ከከተማዋ ሰራተኞች የሚሰጥ ድጋፍ

**8-9** በAlms Houses በኩል ለድሃው የሚደረግ ድጋፍ የሚያሳይ ታሪካዊ ምስል

**10** Cambridge Multi-Service Center (ካምብሪጅ የብዙ አገልግሎት ማዕከል) ሰራተኞች ነዋሪዎች ተግዳሮቶችን ይፈቱ ዘንድ የሚሰጡት እርዳታ

**11** ወረርሽኙ የምግብ ድህንነትን የሚያረጋግጡ አዳዲስ አቀራረቦች እንዲኖሩ አነሳስቷል

**12-13** የካምብሪጅ ፖሊስ በችግር ጊዜ ጣልቃ የመግባት ስልጠና

**14-20** ዋና ዋና የአንቀጽ ሃሳቦች ትርጉሞች


**Cambridgema.gov/digital** ላይ በመሄድ የካምብሪጅ ህይወት እና ሌሎች ሕትመቶችን ዲጂታላዊ ስሪት ያግኙ። ይህ መስተጋብራዊ የሆነ ድህረ-ገጽ ከሕትመት ችግሮች እንደዚሁም ቪድዮዎች እና ሌሎች ፎቶዎችን የተመለከቱ ተጨማሪ እና ወቅታዊ የሆኑ አንቀጾችንም የያዘ ነው።



# ከአዲሱ የከተማ አስተዳዳሪ Yi-An Huang ጋር የተካሄደ የጥያቄ እና መልስ ቆይታ

- የከተማ አስተዳዳሪ በከተማው ምክር ቤት ነው የሚሾመው
- የከተማ አስተዳዳሪ እንደ ከተማዋ ዋና የስራ አስፈጻሚ መኮንን ሆኖ ያገለግላል
- Yi-An Huang በከተማዋ ላይ ከሴፕቴምበር 6፣ 2022 ጀምሮ ሲሰራ ቆይቷል

# ካምብሪጅ አዲስ የከተማ አስተዳዳሪ Yi-An Huang አግኝታለች

"እቺን የምወዳት ከተማን የማገልገል ዕድል ስላገኘው ደስተኛ ነኝ። እኛ እንደ ከተማ የሃይል፣ ብዝሃነት እና ታላቅ ህልም ባለቤቶች ነን - በዚህ ሃላፊነት ላይ መቀመጥ ታላቅ ክብር ነው።"
የከተማ አስተዳዳሪ Yi-An Huang

## የካምብሪጅ ከተማ አስተዳዳሪነት ሃላፊነትን ስታስብ በጣም ፍላጎት እንዲያድርብህ ያደረጉህ የተወሰኑ ነገሮች ምንድን ናቸው?

እቺን የምወዳት ከተማን የማገልገል ዕድል ስለማግኘት ሳስብ ነበር እጅጉን የተደሰትኩት። በካምብሪጅ ህዝባዊ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚማሩ ሶስት ልጆች አሉኝ፣ ይህ ማሕበረሰብም ነው ደግሞ ዕድገታቸውን የሚቀርጸው። መደረግ የሚቻለውን ነገር በማየት እንደሚነቃቁ እና ለሁሉም የተሻለች የምትሆን ከተማ ለመገንባት ብዝሃነት ያለው ማሕበረሰባችንም በጋራ ሲሰራ እንደሚያዩ ተስፋ አደርጋለው።  እኛ እንደ ከተማ የሃይል፣ ብዝሃነት እና ታላቅ ህልም ባለቤቶች ነን - በዚህ ሃላፊነት ላይ መቀመጥ ታላቅ ክብር ነው።

## በካምብሪጅ ማደግ እና ቤተሰብ መመስረት በተመለከተ ደስ የሚሉህ ነገሮች ምንድን ናቸው?

ያደግኩት በቦስተን አከባቢ ነው፣ ነገር ግን ከኮሌጅ ከወጣው ጀምሮ ካምብሪጅ ቤቴ ሆና ቆይታለች። ከትዳር አጋሬ ጋር የተዋወቅነው ትምህርት ቤት ውስጥ ነው፣ የመጀመሪያው ቀጠሮኣችን ደግሞ Au Bon Pain Harvard Square ውስጥ ነው የነበረው። የጋብቻ ጥያቄዬን Weeks Bridge ላይ አቅርቤ፣ ጋብቻችን ደግሞ Memorial Church ነበር የፈጸምነው። ልጆቻችን በከተማ ውስጥ የተወለዱ ሲሆን እኔም ብዙ ውብ የሆኑ ጠዋቶች እና ከሰዓቶች በጣም አስገራሚ በሆኑት ፓርኮቻችን እና የመጫወቻ ሜዳዎቻችን ላይ አሳልፌያለሁ። በተለይም ደግሞ ከBroadway በስተ ሰሜን በኩል ተደብቆ የሚገኘው Paine የጨዋታ መስክን እጅጉን እወደዋለው። ከዚህም በተጨማሪ ይህን ማሕበረሰብ በአጠቃላይ- በዓለማችን ላይ ልዩነት ለመፍጠር የሚሹ ብዙ ሰዎች ያላቸውን ጥልቅ ፍላጎት እጅጉን እወደዋለው። ሃብታም የሆነ የሲቪክ እና የማሕበረሰብ ማዕቀፍ ይገኛል፣ እኔም የዚህ አካል በመሆኔ እጅጉን ደስ ይለኛል።

## በትርፍ ጊዜህ ምን ማድረግ ደስ ይልሃል?

ሶስት ልጆች እና ውሻ አለን፣ በዚህ የተሰነሳ ብዙም ትርፍ የምለው ጊዜ የለኝም! በዚህ የህይወቴ ምዕራፍ፣ የትርፍ ጊዜ ስራዎቼ በጣሙን ተግባር ላይ ያተኮሩ ሆነዋል! ምግብ ማብሰል ደስ ይለኛል፣ ከልጆች ጋር ደግሞ በጣም አስደሳች እየሆነ መጥቷል። ልጅህ በፈገግታ ተሞልቶ እርሱ የሚወደውን ምግብ እንደሰራህለት ሲነግርህ ከመስማት ውጭ ሌሎች ፍሰሃ እንዲሰማህ የሚያደርጉ ጥቂት ነገሮች ናቸው ያሉት። አሁን ላይ ለማገዝ በሚችሉበት የዕድገት ደረጃ ላይ ይገኛሉ። እንቁላል በመጥበስ ጀምረን አሁን ላይ ፓን ኬኮችን ወደ መስራት እየተሸጋገርን ነው፣ በዚህም በቅርቡ በኩሽና ውስጥ ረዳት የምግብ አብሳዮች እንደማገኝ ተስፋ አለኝ።

## የከተማ አስተዳዳሪ ሆነህ በምታሳልፋቸው የመጀመሪያዎቹ ጥቂት ወራት ውስጥ ምን ማሳካት ትፈልጋለህ?

በጣምኡን በስራ የተጨናነቀ በልግ እንደሚሆን አውቃለው! ከከተማዋ ምክር ቤት እና ማሕበረሰብ ጋር ጠንካራ የሆነ የስራ ግንኙነት ለመገባት ጠንክሬ እንደምሰራ ተስፋ አደርጋለው። ብዙ ልንሰራባቸው የሚገቡ ጉዳዮች አሉ፣ እናም ነገሮችን ከግብ ለማድረስ ለመጀመር እጅጉን ብቁ ከሆኑት የከተማችን ሰራተኞች ጋር ለመስራት ደስተኛ ነኝ። ነገር ግን ዋናው ነገር የመረዳት እና የእምነት መሰረት መኖር እንደሆነ አውቃለው። በተለይም ደግሞ ወሳኝ የሆኑ ውሳኔዎችን በምንወስንበት ጊዜ፣ በተለምዶ ወደ ከተማዋ የስብሰባ አዳራሽ የማይመጡ ሰዎች ለመጋበዝ እና በውይይት ላይ ተጨማሪ ድምጾችን እንደማካትት ተስፋ አደርጋለው።

## ካምብሪጅን እየገጠሟት ያሉ ትላልቅ ፈተናዎች እና ያሏትስ ትልልቅ ዕድሎች ምንድን ናቸው ብለህ ታምናለህ?

ከተማን ማስተዳደር እጅጉን ከባድ ነው! ጥልቅ የሆኑ ፈተናዎች እየገጠሙን ይገኛሉ- የመኖሪያ ቤት፣ የአየር ንብረት ለውጥ፣ መጓጓዣ እንደዚሁም የበለጠ እኩልነት ያለበት እና ፍትህ የሰፈነበት ማሕበርሰብ መገንባት። እንዴት ነው ትልልቅ ህልሞችን፣ በአስቸኳይ የሚወሰዱ እርምጃዎችን እና ጠንካራ የሆነ አፈጻጸም ወደ ማምጣት ደረጃ እንዴት ነው ከፍ የምንለው? ይህን ደግሞ እኛ እንደማህረሰብ ወደ ልዩነት እያመራን ሳይሆን ወደ ፊት እየተራመድን እንዴት ነው ልናደርገው የምንችለው? አሁን ላይ እየገጠመን ያለወ ትልቁ ፈተና እና ያለን ትልቁ ዕድል ይህ ይመስለኛል።

## ከቀደመው ስራህ ያካበትከው የስራ ልምድ አሁን ላይ አንተን እንደ አንድ የከተማ አስተዳዳሪ እንዴት ይጠቅመኛል ብለህ ታስባለህ?

በBoston Medical Center ያሳላፍኳቸው ዘጠኝ አመታትን እወዳቸዋለው፣ ከስራ ባህሉ አስገራሚው አካል ደግሞ ራእያችንን ከግብ ለማድረስ የተሻለ ተቋም እንዲሆን በመስራት ላይ ትኩርትን ማድረግ ነበር። በተወሳሰበአሰራር ውስጥ ስንት ነገር እንዳለ እና የመማር፣ ሃላፍነት የመውሰድ እና ቀጣይነት ያለው መሻሻል የሚያመጣ ባህል እንዴት መገንባት እንደሚቻል ተምሬበታለው። በአሁኑ ሰዓት በመሰራት ላይ የሚገኝ ብዙ ትልልቅ ስራ አለ፣ እኔም ይህን መልካም ስራ ለመደገፍ እና ለሁሉም ነዋሪዎቻችን የሚጠቅሙ ውጤቶችን ለማምጣት የሚያስችሉን አዳዲስ ዕድሎችን ለመፈለግ እንደምሰራ ተስፋ አደርጋለው።

## በዚህ አዲስ ሃላፊነትህ ላይ ከመምጣትህ በፊት ከከተማዋ መሪዎች ጋር ስትገናኝ ነበር። እንዴት ነበር?

በክረምት ለነበረኝ ጊዜ፣ አዳዲስ ግንኙነቶችን የመመስረቻ ዕድል በማግኘቴ፣ በተለይም ደግሞ ሁላችንም በጥሩ ስሜት ላይ የነበርን በመሆኑ እጅጉን ደስተኛ ነኝ። በበጋ አጋማሽ መጀመር እጅጉን አስቸጋሪ ይሆን ነበር። ከከተማዋ መሪዎች፣ የከተማ ምክር ቤት እንደዚሁም እኔ ጋር ከማህበረሰቡ ከመጡ ሰዎች ጋር ረጅም ጊዜ ወስጄ ሳዳምጥ እና ስማር ነበር። በጣም መነሳሳትን የሚፈጥር፣ በአሁኑ ጊዜ እየገጠሙን ያሉ ፈተናዎችን ያየሁበት እና ምን ያህል የጋር የምንላቸው ያሉን እሴቶች፣ ግቦች እርስ በእርስ እንዲጣጣሙ የማያደርጉ አንዳንድ ፈተንዎችንም ያስተዋልኩበት ነበር። በዛ ጉዳይ ላይ የበለጠ ለመስራት ተስፋ አለኝ፣ ብዙ ያላገኘኋቸው ሰዎች እንዳሉ ስለማውቅ፣ ወደ ፊት ብዙ ውይይቶች ለማድረግ ፍላጎቱ አለኝ።


## ስለ አመራር ስልትህ እና ከማሕበረሰቡ ጋር እንዴት ባለ መልኩ ለመነጋገር እና ሰራ ለመስራት እንደምታልም ንገርን?

ከተማዋ ከከተማው ምክር ቤት በሚሰጣት አቅጣጫ ላይ ተመርኩሳ ለህዝቦቹ ጥቅም ነው የምትሰራው። እኔ ያለኝ ተስፋ፣ ከተማዋ፣ ማሕበረሰቡ እና የክተማ ምክር ቤቱ፣ አሁን ላይ እየገጠሙን ያሉ ከባባድ ችግሮችን ለመፍታት በሚደረገው ጥረት ውስጥ የአንድ ቡድን አባላት እንደሆኑ እንዲሰማቸው ነው። ይህ ማለት ግን ሁሌም እንስማማለን ማለት አይደለም፣ ነገር ግን በአንድ ጀልባ ውስጥ ተሳፍረን እንዳለን አይነት ስሜት ሊሰማን ይገባል፣ ይህም የጋራ የሚያስማሙ ነገሮችን ለማግኘት መሰራት እና በስተመጨረሻም በአንድ አይነት አቅጣጫ ላይ በጋራ መጓዝ መቻል ማለት ነው። ከማሕበረሰቡ የሚሰጡኝን አስተያየቶች፣ ግብአቶች እና መመሪያ ለመቀበል ተስፋ አደርጋለው- ስህተቶችን እንደምሰራ አውቃለው፣ የሁል ጊዜ አቀራረቤም ደግሞ እውነተኛነት እና ግልጽነት፣ መማር እና ለማሻሻል መሞከር ነው።

# ከአዲሷ የካምብሪጅ Community Safety Department (የማሕበረሰብ ደህንነት መምሪያ) ዳይሬክተር Christina Giacobbe ጋር የተደረገ የጥያቄና መልስ ቆይታ

- ይህ አዲስ መምሪያ የካምብሪጅ በጣም ተጋላጭ ነዋሪዎችን ለመደገፍ ተለዋጭ፣ ህዝባዊ ያልሆነ የደህንነት ምላሽ ለአመጽ እና የባህርይ ቀውስ ጥሪዎችን በማቅረብ ይረዳል።
- ስለወንጀል፣ የእሳት አደጋ፣ የህክምና ድንገተኛ አደጋ ወይም የባህሪ ጤና ቀውስ ለማሳወቅ ወደ 911 ይደውሉ። ወደ 911 መደወል ሁሌም ይመረጣል ሆኖም ወደ 911 የጽሑፍ መልዕክት መላክም አንድ አማራጭ ነው።
- የስሜት ጭንቀት ወይም ራስን የማጥፋት ሀሳብ ሲኖርብዎ ወደ አዲሱ የስልክ መስመር 988 ይደውሉ ወይም የጽሑፍ መልዕክት ይላኩ።

## ካምብሪጅ የአማራጭ ምላሽ መርሃ-ግብር




### 1. የስልክ ጥሪ

አንድ ቀውስ ያጋጠመው ወይም ቀውስ ሲያጋጥም ያስተዋለ ሰው ወደ 911 ይደውላል።



### 2. ማሰማራት

የካምብሪጅ ከተማ ስምሪት የካምብሪጅ የአማራጭ ምላሽ መርሃ-ግብርን እንደ አንድ አግባብነት ያለው ምንጭ አድርጎ በመጠቀም የእሳት አደጋ፣ ፖሊስ ወይም የተለመደው EMS ከማሰማራት ይልቅ የአማራጭ ምልሽ ሰጪ ቡድንን ያሰማራል።



### 3. ምላሽ

ይህ የአማራጭ ምላሽ ሰጪ ቡድን ሁኔታውን ለመገምገም እና ቀጠሎ የሚሆነውን ነገር ቀውሱ ካጋጠመው ግለሰብ ጋር ሆነው ለመስራት ያላቸውን እውቀት እኛ ተሞክሮ አንድ ላይ ይጠቀማሉ።



### 4. ድጋፍ

ይህ የአማራጭ ምላሽ ሰጪ ቡድን ቀውስ ያጋጠመውን ሰው ከተጨማሪ ድጋፍ ሰጪ አገልግሎቶች ጋር በማገናኘት ክትትል እንዲደረግለት ለማስቻል ያላቸውን የማሕበረሰቡ ምንጮች እውቀት ይጠቀማሉ።

# የከተማውን አማራጭ የምላሽ አሰጣጥ የሙከራ መርሃ-ግብር በማሳየት ላይ

የማህበረሰብ ደህንነት መምሪያው ተጋላጭ የሆነውን ህዝብ ዒላማ ያደረጉ ቁልፍ መርሃ-ግብሮች እና አገልግሎቶችን በማቅረብ የማህ በረሰቡን ደህንነት የሚያሻሽሉ በማህበረሰቡ የሚመሩ መፍትሔዎችን ያስተባብራል።

አዲሱ የማህበረሰብ የደህንነት መምሪያ (CSD) መርሃ-ግብሮችን የሚያስተባብሩ እና የባህሪ ጤና ቀውስ (የአዕምሮ ጤና፣ የእድገት እክሎች፣ እና የአደንዛዥ ዕፅ ተጠቃሚነት) ፣የጥቃት መከላከል እና ጣልቃ ገብነት እንዲሁም አጠቃላይ ደህንነት ላይ የሚያተኩሩ ቁልፍ የሆኑ የማህበረሰብ አገልግሎቶችን የሚሰጡ የህዝብ ያልሆኑ የደህንነት ሰራተኞችን ያቅፋል። በተጨማሪም CSD፣ የመስክ ቡድኖች ሁከት-አልባ እና የባህሪ ጤና ቀውስን በተመለከተ ለሚደረጉ ጥሪዎች ምላሽ የሚሰጡበት አማራጭ የምላሽ አሰጣጥ የሙከራ መርሃ-ግብር በዚህ በልግ ያስጀምራል ወደ 911 መደወል ሁልጊዜ ተመራጭ ቢሆንም መደወል በማይቻልበት ጊዜ ወደ 911 የጽሑፍ መልዕክት መላክ ይቻላል። አዲሱ የ 988 መስመር የስሜት ጭንቀት፣የባህሪ መቃወስ፣ ራስን የማጥፋት ስሜት ላጋጠማቸው ወይም ስለሚወዱት ሰው የተጨነቁ ነገር ግን እንዴት ያንን ሰው መደገፍ እንዳለባቸው ለማያውቁ በሙሉ ይገኛል።

---

### የማህበረሰብ የደህንነት መምሪያ ምንድነው? ከተማውስ ይህን እየፈጠረ ያለው ለምንድነው?

የማህበረሰብ የደህንነት መምሪያ ነባር የካምብሪጅ የጤና ደህንነት ኤጀንሲዎች እና ሌሎች መምሪያዎች የሚሰሩዋቸውን ጠቃሚ ስራዎች የሚያሟላ ራሱን የቻለ ክፍል ነው። እንደሌሎች የማህበረሰብ ደህንነት ኤጀንሲዎች እና መርሃ-ግብሮች ሁሉ፣ CSD ጉዳት ቅነሳ እና ሁሉም ሰው ክብር፣ ራስን በራስ ማስተዳደር እና እድል ሊኖረው ይገባዋል በሚል እምነት ላይ የተመሰረቱ የአሰቃቂ የበፊት ታሪክ መረጃዎች መርሆች ላይ የተመሰረቱ በመረጃ የተደገፉ አገልግሎቶችን ለመስጠት ይፈልጋል።

ከተማው ይህን መርሃ-ግብር የሚያቋቁመው ከትጥቅ ውጭ ያሉ የምላሽ አሰጣጥ መርሃ-ግብሮችን ለሚያዘጋጀው የከተማው የምክር ቤት መምሪያ ምላሽ ለመስጠት እንዲሁም ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ የካምብሪጅ ነዋሪዎችን ስለመደገፍ እና ጥቃት የመከላከል ጥረቶችን በተመለከተ ማህበረሰቡ ላይ ላለው ስጋት ምላሽ ለመስጠት ነው።

### አዲሱ የ988 መስመር ቁጥር ምንድነው እና መቼ ጥቅም ላይ መዋል አለበት?

ሰዎች አሁንም ስለወንጀል፣ ስለ እሳት አደጋ ፣ ስለ የህክምና ድንገተኛ አደጋ ወይም ስለ የባህሪ ጤና ቀውስ ለማሳወቅ ወደ 911 መደወል ይችላሉ። የስሜት ጭንቀት ወይም ራስን የማጥፋት ቀውስን የተመለከቱ ወይም ማንኛውም ይህን ካጋጠመው ሰው ለሚደረጉ ጥሪዎች እንዲውል አዲስ የ988 መስመር ሀምሌ ላይ ተጀምሯል። የ988 መስመር ቁጥር ስለሚወደው ሰው የተጨነቀ እና የዛ ሰው ደህንነት እንዲረጋገጥለት ወይም እርዳታ እንዲደረግለት ለሚፈልግ ሰው ጥቅም ላይ መዋል ይችላል። የህክምና ባለሙያ ያልሆኑ፣ የሰለጠኑ አማካሪዎች ለሁሉም ደዋዮች ነፃ፣ ሚስጥራዊ የስሜት ድጋፍ ለመስጠት ይገኛሉ። የ988 ማዕከላት እንደአስፈላጊነቱ የድንገተኛ ጊዜ ወይም አማራጭ ምላሽን ለማስተባበር ከአከባቢው የ911 ማዕከላት ጋር በቅርበት ይሰራሉ። በተጨማሪም፣ ሰዎች የከተማው ከአደጋ ጊዜ ውጪ ቁጥር 617-349-3300 ላይ መደወል ይችላሉ።

### የማህበረሰቡ የደህንነት መምሪያ ለማህበረሰቡ የሚሰጡ አገልግሎቶችን እንዴት ያሻሽላል?

CSD በማህበረሰቡ ተሳትፎ፣ በትኩረት ቡድኖች፣በመረጃ ትንተና፣ እንዲሁም ተጋላጭ ለሆነው ህዝብ የአገልግሎት ክፍተቶችን የሚለይ የተማክሮ ቡድን በማቋቋም ተጨማሪ መርሃ-ግብሮችን እና አገልግሎቶችን ለማዘጋጀት ከአከባቢው ለትርፍ ያልተቋቋመ፣የማህበረሰብ የደህንነት ኤጀንሲዎች እና ሌሎች የአከባቢው አጋሮች ጋር ይተባበራል። እነዚህ አገልግሎቶች የጋራ የመረዳጃ አገልግሎቶች እና ማህበረሰቡን መሰረት ያደረገ የክህሎት ግንባታ እና ስልጠና ማቅረብ እንዲሁም የባህሪ ጤና ችግር ላጋጠማቸው የማህበረሰብ አባላት የድህረ እንክብካቤ እና ንቁ ማህበረሰባዊ ምላሽ መስጠትን ያካትታሉ።

### ምላሽ የሚሰጠው ፖሊስ ወይም CSD መሆኑ እንዴት ይወሰናል?

የክስተት ቦታው ላይ የደህንነት ስጋት የሌለባቸው ሁከት-አልባ የቀውስ ጥሪዎች በCSD ምላሽ ይሰጥባቸዋል። ነገር ግን፣ እንደሁሉም የድንገተኛ ጊዜ አገልግሎት እቅዶች ሁሉ፣ በክስተት ቦታው ላይ የሁሉም ደህንነት መጠበቅ ቅድሚያ የሚሰጠው ነው። የክስተት ቦታው ላይ የጦር መሣሪያ ወይም አስጊ ሁኔታ ሊኖር የሚችልበት የደህንነት ስጋት ካለ በመጀመሪያ ፖሊስ ምላሽ ሰጥቶ ሁኔታውን ካረጋጋ በኋላ የሚያስፈልጉ ተጨማሪ ግብዓቶች ስለመኖራቸው ይወሰናል።

### የCSD ሰራተኞች ምን ዓይነት ስልጠና ይወስዳሉ?

የመምሪያው ሰራተኞች እንደ የስራ ድርሻቸው የተለያዩ ስልጠናዎችን ይወስዳሉ። ለአማራጭ የምላሽ አሰጣጥ መርሃ-ግብሮች ምርጥ ልምምድ ናቸው ተብለው ከሚታወቁት ስልጠናዎች መካከል፦ የችግር አያያዝ፣ መባባስን ማስወገጃ ዘዴዎች፣ የበፊት አሰቃቂ ታሪክ መረጃን መሰረት ያደረገ ምላሽ አሰጣጥ፣ አነሳሽ ቃለ-መጠይቅ፣ CIT (የችግር ጊዜ ጣልቃገብነት ስልጠና)፣ ጉዳት ቅነሳ፣ CPR እና የመጀመሪያ እርዳታ፣ የቤት ውስጥ ብጥብጥ መከላከል እና ምላሽ አሰጣጥ፣ የፍላጎቶች ግምገማ እና የደህንነት እቅድ፣ የወጣቶች ተሳትፎ፣ የአቻ ድጋፍ፣ የምስክር ስልጠና፣ የዘር እኩልነት እና የአከባቢው ማህበረሰብ ድርጅቶች እና ግብዓቶች ስልጠና

**በማህበረሰብ የደህንነት መምሪያ ውስጥ ስለመስራት እንዴት የበለጠ ማወቅ እችላለሁ?**

በማህበረሰብ የደህንነት መምሪያ ውስጥ ያሉ ክፍት የስራ መደቦችን ለማየት የከተማውን የስራ ገጽ በ**Cambridgema.gov/jobs**ላይ ይመልከቱ። ለተጨማሪ መረጃ Christina Giacobbe ን **cgiacobbe@cambridgema.gov** ላይ በመሄድ ያነጋግሩ።




# የከተማው ሰራተኞች ለካምብሪጅ ተጋላጭ የሆኑ ማህበረሰቦች ወሳኝ የሆነ ድጋፍ ይሰጣሉ።

- የካምብሪጅ የህዝብ ቤተ-መጻሕፍት በአካልም ሆነ በስልክ የሚረዳ የማህበራዊ ጉዳይ ሰራተኛ አለው። ማህበራዊ ጉዳይ ሰራተኛው እንግሊዝኛ፣ ስፓኒሽ እና ሄይቲ ክሪኦል ይናገራል።
- በካምብሪጅ አረጋውያን ማዕከል ውስጥ የሚገኙ ሰራተኞች የግብዓቶች እና የመረጃ እርዳታ ሊሰጡ ይችላሉ።
- በ911 የጥሪ ማዕከል እና የካምብሪጅ ፖሊስ ውስጥ የሚገኙ ማህበራዊ ጉዳይ ሰራተኞችም እንዲሁ ድጋፍ ይሰጣሉ።

# ቁርጠኝነት ለፍትሐዊ ነት፣ ተደራሽነት እና አካታችነት



ከተማችን ለሁሉም የካምብሪጅ ማህበረሰብ በተለይም በጣም ተጋላጭ ለሆኑት ህዝቦቻችን ሁሉን አቀፍ የሆኑ የመርሃ-ግብር ስብስቦችን ለማቅረብ ያለው ቁርጠኝነት በበርካታ መምሪያዎች ውስጥ የማህበራዊ ጉዳይ ሰራተኞች እንዲጨመሩ አስችሏል።

**የቤተ-መጻሕፍት ማህበራዊ ጉዳይ ሰራተኛ ከነዋሪዎች ጋር በአካባቢያቸው ቅርንጫፍ ወይም በስልክ ይገናኛል።**

የቤተ-መጽሐፍቱን ግብዓቶች ለማግኘት፣ ለመፍጠር እና ለመጠቀም በየዕለቱ በመቶዎች የሚቆጠሩ የማህበረሰቡ አባላት ወደ ካምብሪጅ የሕዝብ ቤተ-መጽሕፍት (CPL) እና ቅርንጫፎች ያመራሉ። ከቤተ-መጽሐፍቱ አዳዲስ ሀብቶች መሀል አንዱ የሆነው፣ በማርች 2021 የተደረገው የማህበራዊ ጉዳይ ሰራተኞች መጨመር ከተማው ለፍትሐዊነት፣ ተደራሽነት እና አካታችነት ያለውን ቁርጠኝነት ያሳያል። እንዲሁም የማህበረሰቡ አባላት የመሰብሰብ ዝንባሌ ያላቸው ቦታዎች ላይ ግብዓቶችን ስልታዊ በሆነ መንገድ በማኖር ድጋፍ ለመስጠት የሚደረግ የከፍተኛ ሙከራ አካል ነው።

በCentral Square ቅርንጫፍ ቤተ-መጻሕፍት የምትገኘው ፈቃድ ያላት ክሊኒካል ማህበራዊ ጉዳይ ሰራተኛ የሆነችው Marie Mathieu፣ የማህበረሰቡ አባላትን በየቅርንጫፉ የምታገኝ ሲሆን እንግሊዝኛ፣ ስፓኒሽ እና ሄይቲ ክሪኦል ትናገራለች። ባለፈው ዓመት ውስጥ ውስብስብ የስርዓት ድሮችን በማሰስ ለጥቅማ ጥቅሞች እና ድጋፎች እንዲመዘገቡ ከ300 በላይ ደንበኞችን ረድታለች። እነዚህ ስርዓቶች ብዙውን ጊዜ ህይወት አድን የሆኑ ግብዓቶች እጅግ የሚያስፈልጋቸው ማህበረሰቦች ጋር እንዳይደርሱ የማይታለፍ መሰናክል የሚሆኑ ናቸው። በተጨማሪም Marie ደንበኞች ወሳኝ የሆኑ የምግብ እና የአዕምሮ ጤና ግብዓቶችን እንዲያገኙ እና ለመኖሪያ ቤት እና ስራዎች እንዲያመለክቱ ረድታለች። አራት ተለማማጅ ሠራተኞች የቤተ-መጻሕፍቱን ማህበራዊ አገልግሎቶች የሚያሟሉ ሲሆን የማህበረሰብ አባላት ለሳምንታዊ የመግቢያ ጥሪዎች እንዲመዘገቡ የሚያስችለውን የእንክብካቤ ጥሪ ተነሳሽነት በመሞከር ረገድ አስተዋጽኦ አድርገዋል። ከዚህም በተጨማሪ Marie የCPL (ካምብሪጅ የህዝብ ቤተ-መጽሐፍት) ሰራተኞች እንዴት ለተጋላጭ ማህበረሰቦች ድጋፍ መስጠት እንደሚችሉ በማሰልጠን ቤተ-መጽሐፍቱ የተቸገሩትን መርዳት የሚችልበትን አቅም አስፍታለች።

**የካምብሪጅ ፖሊስ ማህበራዊ ጉዳይ ሠራተኞች፣ የፖሊስ መኮንኖች ተጋላጭ ከሆኑ ማህበረሰቦች ጋር የሚሰሩት ስራ ላይ ድጋፍ ይሰጣሉ።**

የካምብሪጅ ፖሊስ ክፍል (CPD) ክሊኒካል ድጋፍ ክፍል (CSU) ሁለት ፈቃድ ያላቸው ክሊኒካል ማህበራዊ ጉዳይ ሠራተኞች አሉት። Elana Klein እና Sabrina Voegelin የስነ-ልቦና ባለሙያ እና CSU ዳይሬክተር ከሆኑት ዶ/ር James Barrett ጋር በመሆን በተለይም የቤተሰብ እና ማህበራዊ ፍትህ ክፍል ውስጥ በቀጥታ ከነዋሪዎች እና ቤተሰቦች ጋር ለሚሰሩ መኮንኖች ወሳኝ የሆነ ድጋፍ ይሰጣሉ። የCSU ሰራተኞች መደበኛ ስልጠና ይሰጣሉ፣ አንዳንድ የጤና ሁኔታዎች በሰው ባህሪ ላይ እንዴት ተፅዕኖ እንደሚያሳድሩ መኮንኖች እንዲረዱ ያግዛሉ እንዲሁም የማህበረሰብ የመከላከል መርሃ-ግብሮችን ይደግፋሉ።

***ጀርባ ገፅ ላይ የሚገኘው ፎቶ፦*** *የCOA ዋና ዳይሬክተር Susan Pacheco (በስተ ቀኝ) እና የCOA የደንበኞች አገልግሎት ዳይሬክተር Vincent McCarthy (በስተ ግራ) ለአረጋውያን ማዕከል ደንበኛ ሰላምታ እየሰጡ።* ***(ከላይ):*** *የቤተ-መጻሕፍት ማህበራዊ ጉዳይ ሰራተኛ Marie Mathieu ከደንበኛ ጋር ሲገናኙ።*

CSU ለነዋሪዎች በተለይም ከመኮንኖች ጋር በቀጥታ ለሚገናኙ ወይም ወደ መምሪያው ለሚላኩ ተጋላጭ ማህበረሰቦች በቀጥታ ይደርሳል። የCSU ዋና ግብ በወንጀል ፍትሕ ስርዓት ውስጥ የመሳተፍ አደጋ ላይ ካሉት ጋር አብሮ በመስራት ትኩረታቸውን ከእስር ቤት በማዞር ወደ አስፈላጊ ድጋፍ እና አገልግሎቶች እንዲሄዱ ማድረግ ነው። በዚህ ባለፍነው ዓመት የCSU ሰራተኞች ከ900 በላይ ልዩ ጉዳዮች ላይ ሰርተዋል።

**የአደጋ ጊዜ ግንኙነት ማህበራዊ ጉዳይ ሰራተኛ ወደ 911 የሚደረጉ አንዳንድ ጥሪዎችን በተመለከተ ጥሪ ተቀባዮችን ይረዳል።**

የከተማው የድንገተኛ ጊዜ ግንኙነት መምሪያ ለተቸገሩት ወቅታዊ እርዳታ ለመስጠት ቆርጦ ተነስቷል። እንዲሁም የድንገተኛ ጥሪ ማዕከል ውስጥ ወደ 911 የሚደረጉ ጥሪዎችን እና የአይምሮ ጤናን የሚያካትት ድንገተኛ ያልሆነ የጥሪ መስመርን በማስተናገድ ጥሪ ተቀባዮችን እንዲያግዝ ፈቃድ ያለው የማህበራዊ ጉዳይ ሠራተኛ አስገብቷል።

**የካምብሪጅ አረጋውያንን ከማህበራዊ አገልግሎቶች ጋር ማገናኘት**

የካምብሪጅ በዕድሜ የገፉ (COA) ደንበኞች አገልግሎት ቡድን እድሜው 60 እና ከዛ በላይ የሆነ ማንኛውም የካምብሪጅ ነዋሪ የሚያስፈልገውን ግብዓት ማግኘት እንዲችል የሚረዳ የጉዳዮች አስተዳደር አካሄድ ወስዶ ይሰራል። COA የተለያዩ ማህበራዊ-ተኮር አገልግሎቶችን ይሰጣል። ምንም እንኳን በቀጥታ ክሊኒካዊ ወይም የህክምና አገልግሎቶችን ባይሰጥም የCOA ሠራተኛ እነዚህን አገልግሎቶች ወደሚሰጡ የአከባቢው ኤጀንሲዎች አረጋውያንን መላክ ይችላል።

የCOA ሰራተኛ ከአረጋውያን ጋር በሚገናኝበት ጊዜ የመኖሪያ ቤት ግብዓቶች፣ የምግብ አቅርቦት፣ የአይምሮ ጤና ወይም የግንዛቤ ድጋፍ፣ የገንዘብ አስተዳደር ወይም የህክምና አገልግሎት ጥቅም ማግኘት ስለመቻሉ ለመወሰን የደንበኛውን እያንዳንዱን የግል ሁኔታ በጥንቃቄ ይመረምራል። ሠራተኛው አረጋዊው ከጤና ወይም ደህንነት ጋር በተያያዘ ግብዓቶች እንደሚያስፈልጋቸው ከወሰነ የሰመርቪል-ካምብሪጅ የአረጋውያን አገልግሎት፣ በካምብሪጅ ቤቶች ባለስልጣን የአረጋውያን መኖርያ ውስጥ የሚሰሩ ፈቃድ ያላቸው ማህበራዊ ጉዳይ ሰራተኞች፣ የካምብሪጅ የፖሊስ መምሪያ ወይም የግዛቱ የጥበቃ አገልግሎትን ጨምሮ ከማህበረሰብ አጋሮች ጋር ያስተባብራል።


የCOA ዋና ዳይሬክተር Susan Pacheco "ግባችን አረጋውያን ራሳቸውን የመቻል ደረጃ እና ጥራት ያለው ህይወትን ጠብቀው መኖር እንዲችሉ ነው" ብለዋል። "በተጨማሪም ለአረጋዊያን ቀጣይነት ያለው ማህበራዊ ድጋፍ በመስጠት ላይ እናተኩራለን። ሰዎች ሲገለሉ አካላዊ እና አዕምሯዊ ጤንነታቸው በፍጥነት ያሽቆለቁላል፤ በመሆኑም ግንኙነት ለደህንነታቸው ወሳኝ ነው"

# The Cambridge Almshouses and Avon Home for Children (የካምብሪጅ የችግርተኞች መጠለያዎች እና የአቮን ቤቶች ለህፃናት)

A
የድሆች እንክብካቤ ታሪካዊ እይታ

በአብዮታዊው ጦርነት ሳቢያ በኒው ኢንግላንድ የእንግሊዝ ሰፈራ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ የተቸገሩ ሰዎች ለእርዳታ ወደቤተሰቦቻቸው፣ ጎረቤቶቻቸው እና ቤተ-ክርስቲያናቸው ይሄዱ ነበር። ምንም ድጋፍ የሌላቸው የከተማው ኃላፊነት ሆኑ፤ ልጆች እንደተለማማጆች ወይም አገልጋዮች ሊወሰዱ አዋቂዎች ደግሞ የጉልበት ስራ ተቀጥረው ሊሰሩ ይችላሉ። ጦርነት እና የገንዘብ ውድቀት ብዙዎችን ለድህነት ዳረጋቸው፤ ትንንሽ ከተማዎችም ድሆቻቸውን ወደ የችግርተኞች መጠለያዎች (የድሆች ቤቶች) እና ወደ ከተማ እርሻ ቦታዎች መሰብሰብ ጀመሩ።

የካምብሪጅ የመጀመሪያዎቹ ሁለት የችግርተኞች መጠለያዎች በነባር ህንጻዎች ውስጥ ይገኙ ነበር፦የመጀመሪያው በ1779 በHarvard Square ሲሆን ተከታዩ ደግሞ በ1786 North Cambridge ነበር። ሶስተኛው በ1818 በአሁኑ Sennott Park አቅራቢያ የተገነባው በ1836 ተቃጥሏል። አራተኛው ከተማው በገዛው መሬት ላይ በ1838 ተገነባ። በCharles River ዳር ከWestern Avenue እስከRiver Street ድረስ ያለው 11 ሄክታር መሬት የችግርተኞች መጠለያን እና የከተማ እርሻን ያስተናግዳል። የንብረቱ ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ ጨመረ። እናም በ1849 ከተማው በጡብ የተገነባውን መጠለያ ቤት የRiverside Press እስኳል ወደሚሆነው መጽሐፍት ማምረቻነት ለቀየረው አሳታሚ ሸጠው።



*የመጠለያ ህንፃው አሁንም በ 45 Matignon Avenue ላይ ቆሞ የሚገኝ ሲሆን ከ2005 ጀምሮ ለÉcole Bilingue መኖሪያ ሆኖ ቆይቷል። ፎቶ ca. 1969.*
የካምብሪጅ ታሪካዊ ኮሚሽን። የሠራተኞች ፎቶ

*የካምብሪጅ መጠለያ ሙሉ እይታ (በስተቀኝ) እና የከተማ እርሻ ፎቶ ca. 1900.*
የካምብሪጅ ታሪካዊ ኮሚሽን። ካልታወቀ ምንጭ።



አዲስ የከተማ እርሻ Alewife እና Tannery Brooks አቅራቢያ ተከፈተ። ከተማው F አዲስ የድሆች ቤት እንዲሰራ የእስር ቤት መሻሻል እንቅስቃሴ መሪ ለነበሩት ለቄስ Louis Dwight ቡድን እና Gridley J. ውል ሰጠ። Bryant፣ የተዋጣለት የቦስተን አርክቴክት። በ1851 የተጠናቀቀው አዲሱ ህንጻ በመጠለያው ነዋሪዎች በተጠረቡ ግራጫ-አረንጓዴ እና ብርቱካናማ ቡኒ ድንጋዮች የተገነባ ነው። ዋናው ማዕከል ቢሮዎችን እና የጋራ ክፍሎችን ይዟል። ወንዶች እና ሴቶች ተለይተው ነበር። በተለያየየህንጻው ክንፍ ይተኙ፣ ለየብቻ የተዘጋጁ አውደ-ጥናቶች ላይ ይሳተፉ እንዲሁም በሁለት የተለያየመመገቢያ ክፍሎች ውስጥ ይመገቡ ነበር። ተቆጣጣሪው (ወይም ጠባቂው) እና ቤተሰቡ በሶስተኛው ክንፍ ውስጥ የግል ክፍሎች እና መኝታ ቤቶችን ያዙ።

አቅም ያላቸው ነዋሪዎች የቤት ውስጥ ተግባራት፣ እርሻ፣ ድንጋይ ቁፋሮ እና ቆሻሻ ማውጣት ላይ መስራት ይጠበቅባቸው ነበር። ጉልበታቸው መጠለያውን ጠብቆ ለማቆየት እንዲሁም ለሚጎበኛቸው ሐኪም፣ ነዳጅ እና ከአካባቢው ስጋ ቤቶች ለሚመጣ ስጋ ለመክፈል ረድቷቸዋል።

በ1913፣ የመጠለያው ነዋሪዎች በዋናነት አዛውንቶች እና ህመምተኛ ድሆች ነበሩ። እርሻው የሚንቀሳቀሰው በኪሳራ ነበር። መጠለያው፣ ለአረጋውያን እና አቅመ-ደካሞች የከተማው መኖሪያ ተብሎ ስሙ ተቀየረ እንዲሁም የሆስፒታል መገልገያዎች ተጨመሩ። (በኋላ፣በ650 Concord Avenue አሁን Neville Place ተብሎ የሚጠራው ቦታ ላይ አዲስ የከተማ መኖሪያ ከFresh Pond ፊት ለፊት ተገነባ። የድሮው መጠለያ ቤት በ1929 ለቦስተን ሊቀ-ጳጳስ ተሸጦ የነበረ ሲሆን እሱም በ2005 ለቦስተን ዓለም-አቀፍ ትምህርት ቤት ተሸጠ።

## የካምብሪጅ የAvon መኖሪያ የህጻናት መጠለያ

James Huntington፣ Harvard Square በሚገኘው የጌጣጌጥ መሸጫው እና Avon Hill Street በሚገኘው ቤቱ መካከል ሲራመድ በየዕለቱ ለሚያጋጥሙት የተቸገሩ፣ ወላጅ-አልባ ህጻናት ያዝን ነበር። በሜይ 1874፣ ሙሉ በሙሉ የተዘጋጀ ፣10 ልጆችን የሚይዝ ቦታ ያለው የህጻናት ማሳደጊያ 32 Avon Hill Street ላይ ገነባ።

Huntington ተቋሙን ለብቻው ጠብቆ ማቆየት አልቻለም። በኖቬምበር 1874፣ የመኖሪያውን አስተዳደር ገንዘብ ለሚያሰባስብ፣ መመሪያዎችን ለሚያወጣ እና የቤት ውስጥ ስራዎችን ጭምር ለሚያከናውን የባለአደራዎች ቦርድ አስተላለፈ። የካምብሪጅ ተማሪዎች ገንዘብ፣ ምግብ፣ የቤት እቃዎች፣ መጻሕፍት፣ መጫወቻዎች እና የሀገር ጉብኝት ሽርሽር ለገሱ። የአከባቢው አነስተኛ ሆቴል አገራባች መሬቱን ለመጫወቻ ቦታነት አበረከተ። አስተዳደሮቹ የቤተሰባዊነት ስሜት ያለው አከባቢን መፍጠር በመፈለጋቸው ህፃናቱ ትምህርት ቤት እንዲሄዱ እና የእሁድ ትምህርት እንዲያገኙ እንዲሁም ከአከባቢው የጤና ባለሙያዎች ነፃ የጤና እንክብካቤ እንዲያገኙ አመቻቹ። በ1879 ፣ ለ15 ተጨማሪ ህፃናት ክፍል የያዘ ባለሶስት ፎቅ ክንፍ መኖሪያው ላይ ተጨመረ ሆኖም ያለው ፍላጎት ከሚገኘው ቦታ በላይ መጨመሩን ቀጠለ።




*የ2018፣ የ32 Avon Hill Street እይታ፣ Huntington ለህጻናት ማሳደጊያ ነት የገነባው ቤት (በኋላ የAvon መኖሪያ ተብሎ የሚጠራው)*

የካምብሪጅ ከተማ ንብረት የመረጃ ቋት።



*የAvon መኖሪያ በ1000 Mass. Ave ጀርባ በሚገኘው ትልቅ ግቢ ውስጥ ለአከባቢው ህጻናት የመጫወቻ ሜዳ ከፈተ።*




*የAvon Home የመጨረሻው አድራሻ 1000 Massachusetts Avenue ነበር። ህንጻው በ1975 ፈረሰ።*

የካምብሪጅ ታሪካዊ ኮሚሽን። 55ኛው የAvon Home ዓመታዊ ሪፖርት፣ 1929.

በ1889፣ ስኬታማ የገንዘብ ማሰባሰቢያ ዘመቻ የAvon መኖሪያ በ309 Mt. Auburn Street ላይ አዲስ ሰፊ ህንጻ እንዲከፍት አስቻለው። የእንክብካቤ ሞዴሎች እየተሻሻሉ ሲሆዱ፣ መኖሪያው የማደጎ የሙከራ መርሃ-ግብር ጀመረ። አዲሱ አካሄድ በጣም ውጤታማ እና ስኬታማ ከመሆኑ የተነሳ በ1913፣ ባለአደራዎቹ የህጻናት ማሳደጊያውን ለመዝጋት እና እንደ የህጻናት ምደባ ኤጀንሲ ብቻ ለመስራት ድምጽ ሰጡ። ከአስር ዓመታት በኋላ ድርጅቱ 1000 Massachusetts Avenue ላይ የAvon Hill ማህበረሰብ ማዕከልን ከፈተ። ድርጅቱ የማደጎ ስራውን ቀጥለእንዲሁም በአውደ-ጥናቶች እና በአዲሱ የመጫወቻ ሜዳ እንዲዝናኑ የሰፈር ህጻናትን ጋበዘ።

በ1945፣ የማህበረሰብ ማዕከሉ ተዘጋ፣ ቢሮዎቹም ወደ Church Street ተዛውረው ኤጀንሲው የማህበረሰብ አገልግሎቶቹን ማሳደግ ቀጠለ። በ1965፣ የAvon መኖሪያ፣ ለህጻናት ጥብቅና በመቆም የተረጋጋ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ፍቅር ያለበት ቤት ውስጥ መኖራቸውን እያረጋገጠ የቀጠለው የካምብሪጅ የቤተሰብ እና የህጻናት አገልግሎቶች፣ የአሁኑ Bridges Homeward አካል ሆነ።

# የካምብሪጅ ባለብዙ አገልግሎት ማዕከል ሰራተኞች፣ ነዋሪዎች የመኖሪያ ቤት መሰናክሎችን እንዲወጡ እና ወሳኝ ግብዓቶችን ማግኘት እንዲችሉ ይረዳሉ።



- የባለብዙ አገልግሎት ማዕከሉ የቤት እጦት ላይ ያሉ ሰዎችን ይረዳል እንዲሁም ሰዎች በቤታቸው ውስጥ እንዲቆዩ ለመርዳት ከቤት የመፈናቀል መከላከል ድጋፍ ይሰጣል።
- ሰራተኞች፣ ያሉትን ጥቅማጥቅሞች ደንበኞች እንዲያገኙ ለመርዳት የእያንዳንዳቸውን ግላዊ ሁኔታ ያዳምጣሉ።
- MSC (ባለብዙ አገልግሎት ማዕከል) ከከተማ እና የማህበረሰብ አገልግሎቶች ጋር የሚያገናኝ ማዕከል ነው።

በ362 Green Street የሚገኘው የካምብሪጅ የባለብዙ አገልግሎት ማዕከል (MSC)፣ የቤት እጦት ለገጠማቸው፣ ከቤት መፈናቀል ለተጋረጠባቸው፣ ፈታኝ የመኖሪያ ቤት ሁኔታዎች ውስጥ ለሚገኙ ግለሰቦች እና ቤተሰቦች ቀጥተኛ አገልግሎቶችን ይሰጣል። በዓመት እስከ500 የሚደርሱ ቤተሰቦችን የሚያገለግለው MSC፣ ደንበኞች ለህዝብ ለሚሰጡ ጥቅማጥቅሞች እንዲያመለክቱ፣ የህግ ድጋፍ እና የገንዘብ ምክር፣ እንዲሁም የአይምሮ ጤንነት እና የአደንዛዥ እጽ አላግባብ ተጠቃሚነት አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ይረዳል።

የMSC ዳይሬክተር Maria Melo፣ “ሰዎች ደህንነት እንዲሰማቸው እና የዕለት ተዕለት ህይወታቸውን እንዲመሩ ለማብቃት የተረጋጋ የመኖሪያ ቤት መኖር ቁልፍ ነው” ብለዋል። “ግለሰቦች የመኖሪያ ቫውቸሮችን እንዲያገኙ እንረዳቸዋለን፣ በመኖሪያ ቤት ፍለጋቸው እንደግፋቸዋለን፣ እንዲሁም የመኖሪያ ቤት መረጋጋትን ከሚያበረታቱ ግብዓቶች ጋር እናገናኛቸዋለን“

የፈMSC ሰራተኞች ሰዎች የመኖሪያ ቤት እንዲያገኙ ለመርዳት ከከተማው የማህበረሰብ ልማት መምሪያ የቤቶች ክፍል፣ ከከተማው የቤቶች ግንኙነት ቢሮ፣ ከካምብሪጅ የቤቶች ባለስልጣን እና ሌሎች የአከባቢው የቤት አቅራቢዎች ጋር በቅርበት ይሰራሉ። በአካል የመኖሪያ ቤቶች ፍለጋ አውደ-ጥናት ሁልጊዜ ማክሰኞ ከሰዓቱ 02:30 እስከ 05:00 ድረስ ይሰጣል፤ ተሳታፊዎች ስለአከባቢው የመኖሪያ ቤት አማራጮች ያውቃሉ እንዲሁም ድጎማ የሚደረግላቸው የመኖሪያ ቤት ጠባቂዎች ዝርዝር ውስጥ ለመካተት ያመለክታሉ። ለመመዝገብ፣ 617-349-6338 ላይ ይደውሉ።

የMSC ሰራተኞች ደንበኞች በመኖሪያ ቤት የማግኘት ሂደት ውስጥ የሚያጋጥሟቸውን መሰናክሎች እንዲወጡ መርዳት ይችላሉ። ለምሳሌ፣ ቤት እጦት ያጋጠመው ግለሰብ፣ ለመኖሪያ ቤት ቫውቸር ብቁ ለመሆን የመታወቂያ ካርድ ከሌለው ይህን ለማግኘት የሚያስፈልገውን የ25 ዶላር ክፍያ MSC መሸፈን ይችላል። እንዲሁም የቤት እጦት ያለባቸውን ግለሰቦች እና ቤተሰቦች ክፍት ቦታ ወዳላቸው መጠለያዎች ሊመሩ ይችላሉ።

የMSC ስራ ዋና ገጽታ በቤት እጦት እና ከቤት የመፈናቀል መከላከል ላይ ያተኩራል፤ እና ሰራተኞቹ ደንበኞች ጥቅማጥቅሞችን ሙሉ በሙሉ መጠቀማቸውን ለማረጋገጥ የእያንዳንዳቸውን ግላዊ ሁኔታ ይገመግማሉ። “በሁሉም የስራ ቀናት ያለቀጠሮ የመስተናገጃ ሰዓታትን እናቀርባለን። ያጋጠምዎት ምንም ይሁን ምን፣ ስለሁኔታዎ የሚያናግርዎት የጉዳይ አስተዳደር አለ” ይላሉ Melo። “ሀሳብዎ የሚደመጥበት ሁሉንም በአንድ የሚያገኙበት ስፍራ ነን”።

እንደ የሰብዓዊ አገልግሎት መርሃ-ግብር መምሪያ ክፍል፣ MSC ደንበኞችን በፍጥነት ከነዳጅ እርዳታ፣ የካምብሪጅ የቅጥር መርሃ-ግብር እና የህፃናት እንክብካቤ ግብዓቶችን ጨምሮ ከአጋዥ የከተማ እና የማህበረሰብ አገልግሎቶች ጋር ለማገናኘት የሚገኝ ድርጅት ነው።

MSC ከሌሎች የከተማ መርሃ-ግብሮች ሪፈራል ያገኛል እና ደንበኞችን ከማህበረሰቡ አገልግሎት ሰጪዎች ጋር ያገናኛል። ለምሳሌ ደንበኞች ኪራይ ሳይከፍሉ ከዘገዩ፣ MSC ለበጀት እገዛ ወደ Just-A-Start ነፃ የገንዘብ ዕድሎች መርሃ-ግብር ሊመራቸው ይችላል። ደንበኞች ህጋዊ ችግሮች እያጋጠሟቸው ከሆነ የMSC ሰራተኞች ወደ እንደ Cambridge/Somerville ህጋዊ አገልግሎቶች እና De Novo ላሉ አጋሮች ሊመሯቸው ይችላሉ።

MSC በኢሚግሬሽን ወረቀት ላይ የነፃ እገዛ ወይም ወደ ሌላ የኢሚግሬሽን አገልግሎቶች ሪፈራል በማግኘት ዙሪያ ለካምብሪጅ የሄይቲ ማህበረሰብ ድጋፍ የሚሰጥ የሄይቲ አገልግሎቶች አስተባባሪን በውስጡ ይዟል።

“ደንበኞቻችንን ለመርዳት ከማህበረሰብ አጋሮቻችን ጋር በቋሚነት እየሰራን ነው” ይላሉ Melo። “ይህ ትብብር በተከራይ እና አከራይ መሀል ያለን አለመግባባት እንደ መፍታት ካለ ከፍ ያለ ጥረት አንስቶ እስከ ቤት ለሌለው ደንበኛ ጫማ የማግኘት ዓይነት ትንንሽ መፍትሔዎችን ያካልላል።”

## የባለብዙ አገልግሎት ማዕከል ያለቀጠሮ የመስተናገጃ ሰዓቶች

**362 Green St., Cambridge**

ሰኞ ................................ 9 a.m. – 7:30 p.m.
ማክሰኞ-ሐሙስ ................ 9 a.m. – 4:30 p.m.
ዓርብ ..............................9 a.m. – 11:30 a.m.

**ለተጨማሪ መረጃ፣** 617-349-6340 ላይ ይደውሉ።

# በካምብሪጅ ውስጥ የምግብ ዋስትና ማጣትን በተመለከተ ወረርሽኙ አዳዲስ አካሄዶች እንዲኖሩ ያነሳሳል።




- የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በካምብሪጅ ውስጥ ረሃብ ዋነኛ ችግር መሆኑን አጋልጧል።
- አዳዲስ መርሃ-ግብሮች በተናጠል ለሚገኙ ወይም በለይቶ ማቆያ ለሚገኙ ነዋሪዎች ምግብ ያደርሳሉ።
- የአከባቢው ኤጀንሲዎች የከተማውን የድንገተኛ ጊዜ የምግብ ስርዓት አሻሽለዋል።

በኮቪድ-19 ወቅት የምግብ ወጪ እና ስራ አጥነት በመጨመሩ ብዙ ሰዎችን ለምግብ እጦት ስጋት ዳርጓል። በ2021 ከ8 የካምብሪጅ ነዋሪዎች 1 ሰው የምግብ ዋስትና አልነበረውም።

ከማርች - ሰኔ 2020 ድረስ አብዛኞቹ የምግብ ማከማቻዎች ተዘግተው ቢቆዩም የከተማው የአረጋዊያን ምክር ቤት በማህበረሰቡ የምግብ መስመር ላይ ለአረጋውያን እና በሽታ የመቋቋም አቅም ለሌላቸው ከ1000 በላይ ምግቦችን ካቀረበው Food for Free ጋር በአጋርነት ሰርቷል። በዲሴምበር 2020፣ የካምብሪጅ የህዝብ ጤና መምሪያ በቤት ውስጥ ወይም በለይቶ ማቆያ ተገልለው አንድ ሳምንትና ከዛ በላይ የቆዩና ምግብ ማግኘት የማይችሉ ነዋሪዎችን ለመርዳት ጥረቱን ቀጥሏል።

የካምብሪጅ የህዝብ ጤና መምሪያ የስነ-ምግብ ባለሙያ የሆኑት Rachael Cross, MS፣ RD፣LDN፣ “እነዚህ ነዋሪዎች ወደ ምግብ ማከማቻ ወይም የግሮሰሪ መደብር የሚወጡበት መንገድ አልነበራቸውም እንዲሁም የቤት ውስጥ ምግብ አቅርቦት ክፍያም እጅግ ውድ ነበር” ብለዋል። ካምብሪጅ ኮቪድ ፖዘቲቭ የሆኑ እና ለምግብ እጦት ተጋላጭ የሆኑ ነዋሪዎችን የሚለይ እንዲሁም የምግብ ሸቀጣ ሸቀጦችን እና አቅርቦቶችን በፍጥነት ወደቤታቸው የሚያደርስ ስርዓት አስፈልጓት ነበር።

የጤና መምሪያው ከካምብሪጅ ኢኮኖሚያዊ ዕድሎች ኮሚቴ (CEOC) እና Food For Free ጋር ተባብሯል። በአራት ሳምንታት ውስጥ ቡድኑ እንዲህ ዓይነቱን ስርዓት ጀምሯል። በኮቪድ-19 “የማረጋገጫ” ጥሪዎች ወቅት የህዝብ ጤና የንክኪ ተከታታዮች ምግብ የሚያስፈልጋቸውን ነዋሪዎች ለይተዋል። መረጃው በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ለCEOC ሰራተኞች እንዲደርስ ይደረጋል። እነሱም ምግብ ፣ የስጦታ ካርዶች እና ሌሎች አቅርቦቶችን አሽገው ይልካሉ። Food For Free ምግቦችን ወደ ቤት ያደርስ ነበር።

“በጣም ታምሜ ነበር፣ ወደ ገበያ መሄድም ሆነ ምግብ ማብሰል አልቻልኩም፣ ምንም ማድረግ አልቻልኩም” ስትል አንዲት ባለፈው በልግ በኮቪድ-19 ተይዛ የነበር እና የምግብ ጥቅል ከመርሃ-ግብሩ የተቀበለች ሴት ተናግራለች። “ይህ በገንዘብም ሆነ በስሜት ረገድ ትልቅ እገዛ ነበር“

እስካሁን ከ180 በላይ የካምብሪጅ ቤተሰቦች በዚህ መርሃ-ግብር አማካኝነት የምግብ ጥቅል አግኝተዋል፤ ይህም መርሃ-ግብር በ2022 ከአውራጃው እና ከተማው ጤና ኃላፊዎች ብሔራዊ ማህበር የፈጠራ እና ልምምድ ሽልማት አግኝቷል።

ካምብሪጅ ውስጥ ስላለው ረሃብ እና አዲሱን ፍላጎት ለማሟላት የከተማው የድንገተኛ ጊዜ የምግብ ስርዓት መጠናከር እንደሚገባው ወረርሽኙ አሳይቷል።

*ከላይ የሚገኘው ፎቶ፡- የCEOC ሰራተኞች በኮቪድ-19 ሳቢያ በተናጠል ወይም በለይቶ ማቆያ ለሚገኙ ነዋሪዎች የምግብ ሳጥኖችን ያዘጋጃሉ።*

በ2021 የጤና መምሪያ እና CEOC በአሁኑ ጊዜ ሰባት የምግብ ማከማቻዎችን ያካተተው እና በየዓመቱ ብዙ ሺህ ነዋሪዎችን የሚያስተናግደው የካምብሪጅ የምግብ ክምችት መረብን ለማሻሻል አቀዱ።

የ2021 የካምብሪጅ የምግብ ክምችት መረብ ግምገማ ሪፖርት ደራሲ እና የCEOC የመርሃ-ግብሮች እና የህዝብ መመሪያ ዳይሬክተር Rachel Plummer፣ “ለደንበኞቻችን ክብር በጣም አስፈላጊ ነው” ብለዋል።

CEOC በበልግ 2021 የሰሜን ካምብሪጅ የምግብ ማከማቻውን ሲከፍት ከግምገማው ሪፖርት የተሰጡትን ብዙ ምክረ-ሃሳቦች በውስጡ አካቷል። ተልቅ ያለ ቦታ አለ ማለት ውጪ ላይ የሚሰለፉ ደንበኞች ቁጥር ይቀንሳል ማለት ነው። የምግብ ማከማቻው ረዘም ያሉ ሰዓታትን የሚቆይ ሲሆን ደንበኞች የሚፈልጉትን ምግብ ከመደርደሪያዎች ላይ መምረጥ ይችላሉ።

Food For Free ስርዓቶችን አሻሽሏል፣ ተጨማሪ በጎ ፈቃደኞችን መልምሏል እንዲሁም አዳዲስ የቤት ለቤት ምግብ አቅርቦት መርሃ-ግብሮችን ፈጥሯል። በጥር 2021፣ ኤጀንሲው ከልክ ያለፈውን የምግብ ፍላጎት ለመፍታት *Just Eats* ን ጀመረ። ድርጅቱ መጀመሪያ ላይ በየሳምንቱ ለ500 ቤተሰቦች በታላቁ ቦስተን አከባቢ የምግብ ሳጥኖችን ለማከፋፈል አቅዶ ነበር፣ ሆኖም የምግብ ፍላጎቱ እጅግ ከመብዛቱ የተነሳ በአሁኑ ሰዓት Food For Free በየሳምንቱ ከ4000 በላይ ለሚሆኑ ቤተሰቦች የምግብ ሳጥኖችን እያከፋፈለ ይገኛል።

ይህንን ጥረት የበለጠ ለመደገፍ ከተማው በአሜሪካን የማዳን እቅድ ህግ (ARPA) ገንዘብ መድቧል።

## ምግብ ያስፈልግዎታል?

- የምግብ ዕቃዎችን በዚፕ ኮድ ይፈልጉ: **camb.ma/need-food**
- የካምብሪጅ የምግብ ግብዓቶች መመሪያ **camb.ma/foodguide**

ለካምብሪጅ የምግብ ኤጀንሲ ወይም ማከማቻ በበጎ ፈቃደኝነት ለመለገስ፣ እባክዎ ካምብሪጅ የምግብ ግብዓቶች መመሪያ ውስጥ የሚገኙትን ቡድኖች ያናግሩ።

# ለካምብሪጅ ፖሊስ የችግር ጊዜ ጣልቃ ገብነት ስልጠና እያመጣው ያለው ለውጥ እና ስለ Nelson ታሪክ



- የችግር ጊዜ ጣልቃ ገብነት ስልጠና (CIT) ለሁሉም ደህንነቱ የተጠበቀ ውጤት ወሳኝ ሚና ሊጫወት ይችላል።
- የCIT መርሃ-ግብሮች የአዕምሮ ህመም ያለባቸውን ግለሰቦች ከወንጀለኛ መቅጫ ስርዓት ወደ የጤና እንክብካቤ ስርዓቶች እንዲዛወሩ ያደርጋሉ።
- ብርቱ የCIT መርሃ-ግብሮች ያሏቸው ማህበረሰቦች የከባድ እና ለሞት የሚዳርጉ ክስተቶችን መቀነስ ይመለከታሉ።

